አፍሪካ ቲቪ

9

# አፍሪካ አካዳሚ
## AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች

5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

| | | | |
|---|---|---|---|
| 15 | ያ ሐዩ ያቀዩም ቢረህመቲከ አስተጊስ አስሊህ ሊ ሸዕኒ ኩለሁ ወላተኪልኒ ኢላ ነፍሲ ጦርፈተዐይን፡፡ ህያውና ራሱን ቻይ የሆንከው አምላክ ሆይ፣ በእዝነትህ እታገዛለሁ፡፡ ጉዳዩን ሁሉ አስተካክልልኝ፡፡ ቅጽበትም ያህል ወደራሴው አትተወኝ፡፡ | ጧት 1ጊዜ ማታ 1 ጊዜ | ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ለፋጢማ አደራ ያሏት ዱዓ ነው፡፡ |
| 16 | አላሁመ አፊኒ ፊ በደኒ አላሁመ ዐፊኒ ፊ ሰምዒ አላሁመ ዓፊኒ ፊበሰሪ አላሁመ እኒ አኡዙ ቢከ ሚነል ኩፍር ወልፈቅሪ አላመ ኢኒ አዙዙቢከ ሚን ዐዛቢ ልቀብሪ ላኢላ ኢላህ አንተ፡፡ (አላህ ሆይ ለአካሌ ጤንነትን ለግሰው አላህ ሆይ ጆሮዬን ጤነኛ አድርግልኝ አላ ሆይ አይኔን ጤነኛ አድርግልኝ ካንተ ውጪ ሌላ አምላክ የለም፡፡ አላህ ሆይ ከክህደትና ከድህነት እንዲሁም ከቀብር ውስጥ ቅጣት በአንተ እጠበቃለሁ ካተ ውጪ ሌላ አምላክ የለም) | ጧት 3 ጊዜ ማታ 3 ጊዜ | ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ በዚህ ዱዓ ያደርጉበት እንደነበር ተዘግቧል፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 17 | አላሁመ ኢኒ አስአሉከል ዓፊየተ ፊዲኒ ወዱንያ ወአህሊ ወማሊ አላሁመ ስቱር ዐውራቲ ወአሚን ረውዓቲ አላሁመ ኢህፈዝኒ ሚን በይኒ የደየ ወሚን ኸልፊ ወዐን የሚኒ ወዐን ሺማሊ ወሚን ፈውቂ ወአዑዙ ቢዐዘመቲከ አን ኡግታለ ሚን ታህቲ፡፡ (አሏህ ሆይ በቅርቢቱም ሆነ በመጪዋ አለም ጤንነትንና ምህረትን እለምንሐለሁ አላህ ሆይ! እኔ ምህረትና ጤንነትን እየጥይሃለሁ፡፡ በዚህም ሆነ በተከታዩ አለም አላህ ሆይ! ምህረትንና ጤንነትን በእምነቴ በአለማዊ ሕይወቴ በቤተሰቦቼ በገንዘቤ እጠይቅሃለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ደካማ ጎኔን ሸፍንልኝ፡፡ አላህ ሆይ! ከበስተፊቴ ጠብቀኝ፡፡ ከበስተኋላዬም ጠብቀኝ፡፡ ቀኜንም ግራዬንም ጠብቀልኝ፡፡ ከስሬም ጥቃት እንዳይደርስብኝም በታላቅነትህ እጠበቃለሁ፡፡) | ጧት እና ማታ | ከነቢዩ እንዚህ ዱዓዎችን ጧትና ማታ ያደረጉበት እነደነበር ተዘግቧል፡፡ |
| 18 | ሱብሀነላህ ወቢ ሀምዲሂ ዐደደ ኸልቂሂ ወሪዷ ነፍሲሂ ወዚነተ ዐርሺህ ወሚዳደ ከሊማቲሂ፡፡ (አላህ ሆይ! እንደን አልባ ነህ ምስጋናም ላንተ ነው፡፡ በፍጡራኑ ቁጥር ልክ አንተ በወደድከው ነገር ሁሉ ልክ በአርሽህ ክብደት ልክና በንግግርህ ቀለም መድ (ዘውታሪነት) ልክ፡፡) | ጧት 3 ጊዜ | ከንጋቱ አንስቶ እስከ ምሳ ድረስ አላህን ለማውሳት ከመቀመጥ ይበልጣል |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## ከፍተኛ ምንዳ እንዳላቸው ከነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ሙሐመድ የተነገረላቸው አንደበታዊና ተግባራዊ ጉዳዮች፡፡

| | ተግባሩ | ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተነገረለት መረጃው |
|---|---|---|
| 1 | ላኢላሀ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢንቀዲር | በቀን መቶ ጊዜ ይህን ያለ ሰው አስር ባሪያዎችን ነፃ እንዳወጣ ይቆጠራል፡፡ መቶ ኸይር ስራ ይመዘገብለታል፤ መቶ ወንጀሎች ይታበሱለታል፤ በዚያ ዕለት እስከ ሚመሽ ድረስ ከሰይጣን ጥበቃ ይሆንለታል፡፡ እሱ ከሰራው የበለጠ ከስራ ሰው በስተቀር የሚበልጠው የለም፡፡ |
| 2 | ሱብሐነ አላህ ወል ሐምዱ ሊላህ ላኢላሀ ወኢለህ ወሏሁ አክበር፡፡ | ወደ ሰማይ በሄድኩበት ሌሊት ኢብራሂምን አግኝቼ ነበር፡፡ እናም ሙሐመድ ሆይ! ለህዝቦችህ ሰላምታ አድርስልኝና ጀነት አፈሯ መልካም፤ ውሃዋ ጣፋጭ መሆኗንና እሷ - ስለሆነች አትክልቷ ሱብሐነ አላህ ወል ሐምዱ ሊላህ ወ ላኢላሀ ወሏሁ አክበር መሆኑን ንገራቸው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 3 | ሱብሀነ አላህ አልአዚም ወቢ ሀምዲሂ<br><br>(ሱብሀነ አላህ ወቢ ሀምዲሂ ሱብሀነ አላህል-ዐዚም) ማለት፡፡ | ጧትና ማታ (ሱብሀነ አላህ ወቢ ሀምዲህ) መቶ ጊዜ ያለ ሰው ወንጀሉ የባህር አረፋት ቢሃል እንኳን ይታበስለታል፡፡ እሱ እንዳለው ወይም ከእሱ በላይ ያለ ካልሆነ በስተቀር በቂያማ ዕለት ከእሱ የተሻለ አይመጣም፡፡ ሁለት ቃሎች በምላስ ላይ ቀላሎች በሚዛን ላይ ግን ከባዶች አላህ ዘንድ የተወደዱ ናቸው፡፡ እነሱም (ሱብሀነ አላህ ወቢ ሀምዲህ ሱብሀነ አላህ አል-ዐዚም) |
| 4 | ላሀውለ ወላ ቁወ  ተኢላ ቢላህ | ከጀነት ድልቦች አንዱን ልንገራችሁን? አዎ አልኳቸው፡፡ ላሀውለ ወላ ቁወ ተኢላ ቢላህ ነው አሉ፡፡ |
| 5 | ጀነትን እንዲሰጠው እና ከእሳት እንዲጠብቀው መለመን | አላህን ሶስት ጊዜ ጀነትን እንዲሰጠው የለመነ ሰው ራሷ ጀነት ይህንን ሰው ወደ ጀነት አስገባው ብላ ትለምንለታለች፡፡ አላህን ሶስት ጊዜ እሳትን እንዲጠብቀው የለመነ ሰው ራሷ እሳት ይህንን ሰው ከእኔ ጠብቀው ብላ ትለምንለታለች፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | የውይይት ማሳረጊያ (መደምደሚያ) | በአንድ ቦታ ተቀምጦ ዛዛታው የበዛበት ከቦታው ሳይነሳ (ሱብሃነከ ላሁመ ወቢሐምዲከ አሽሀዱ አላኢላህ ኢላ አንተ አስተግፊሩከ ወአቱቡ ኢለይክ) ያለ ሰው በዚያ ቦታ ላይ የነበረውን ሁሉ ስህተት ያብስለታል፡፡ |
| 7 | 10 አንቀፆች ከሱረትል ከህፍ (የዋሻ ሰዎች ምዕራፍ) አልፎ አልፎ ማንበብ | ከዋሻ ሰዎች ምዕራፍ  አስር አንቀፅን የሐፈዘ ሰው ከደጃል ተንኮል ይጠበቃል፡፡ |
| 8 | በነቢዩ ሙሐመድ ላይ ሶለዋት ማውረድ | አንድ ጊዜ በእኔ ላይ ሶለዋት ያወረደ ሰው በእሱ ላይ አላህ አስር ጊዜ ሶለዋት ያወርድለታል፡፡ አስር ወንጀልም ይሰረዝለታል፡፡ አስር ደረጃም ይጨመርለታል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 9 | አንዳንድ የቁርአን አንቀፆችን ማንበብ (መቅራት) | በቀንና በሌሊት አስር የቁርአን አንቀፅን ያነበበ ሰው ከዝንጉዎች አይመዘገብም፡፡ መቶ አንቀፅን ያነበበ ሰው ደግሞ ከቃኒቲን ከፈርሀያኖች ይፃፋል፡፡ ሁለት መቶ ያነበበ ሰው ቁርዓን የቂያማ ቀን በሱ ላይ አይከራከርበትም አምስት መቶ ከቀራ ደግሞ ትልቅ ተራራ የሚያክል አጅር ይፃፍለታል፡፡ |
| 10 | የአዛን አድራጊዎች ምንዳ | የአዛን አድራጊን ድምፅ የሚሰማ ጂን፣ ሰውና ሌላም ይሁን የቂያማ ዕለት ምስክር ነው፡፡ |
| 11 | አዛን አድራጊን መከተልና ከአዛን በኋላ ዱዓ ማድረግ | አዛንን ሰምቶ (አላሁመ ረበ ሀዚሂ ደዕወቲ ታመህ ወሶላቲልቃኢመህ ኣቲ ሙሐመደን አል ወሲለህ ወል ፈዲለህ ወብዐስሁ መቃመን መህሙደን አለዚ ወዐድተሁ) ያለ ሰው የቂያማ ዕለት የእኔን ሽምግልና ያገኛል ብለዋል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 12 | ውዱዕን ማሳመር | ወዱዕን አሳምሮ ያደረገ ሰው ወንጀሉ ከሙሉ አከላቱ ከጥፍሩ ስር ሳይቀር ነው ተመዞ የሚወጣው ብለዋል፡፡ |
| 13 | ከውዱዕ በኋላ ዱዓ ማድረግ | ወዱዕ አድርጎ ያሳመረ ወይም ያዳረሰና ከዚያም አሽሀዱ አላኢላሀ ኢለሏህ ወአነ ሙሀመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ ያለ ሰው ስምንቱ የጀነት በሮች ተከፍተውለት በፈለገው እንዲገባ ይደረጋል፡፡ |
| 14 | ከውዱዕ በኋላ ሁለት ረከዐ መስገድ | ውድዕን አሳምሮ አድርጎ ከዚያም ሁለት ረከዓን በሙሉ ልብ የሰገደ ሰው ጀነት ለእሱ ትሆናለች፡፡ |
| 15 | ወደ መስጂዶች ጉዞን ማብዛት | ወደ መስጂድ የተጓዘ ሰው ሲሄድና ሲመጣ አንዷ እርምጃ ወንጀል ማበሻ ስትሆን ሌላዋ ደግሞ ሐሰና ይፃፍለታል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 16 | ለጁሙዐ ሶላተ መዘጋጀትና መማለድ | ለጁሙዐ ሶላት ያስታጠበና የታጠበ ከዚያም የማለደና በመጓጓዣ ሳይሆን በእግሩ የሄደና ከኢማሙ ቀርቦ ሳያላግጥ ያዳመጠ በየእርምጃው ሌቱን ቁሞ ቀኑን ፁሞ እንዳሳለፈው አንድ አመት ዒባዳ ምንዳ ያገኛል። የጁሙዐ ዕለት ታጥቦና በሚችለው ፀድቶ ቅባቱን ተቀብቶ ወይም ከቤተሰቡ ሽቶ እንኳን ቢሆን ተቀብቶ ወደ መስጊድ የሄደና በሁለት ሰዎች መካከል ሳይለያይ አላህ እንከሚቀጥለው ጁሙዐ ድረስ ያለው ወንጀል ይማርለታል። |
| 17 | የመጀመሪያን የሶላት መግቢያ ተክቢራን ማግኘት | የመጀመሪያን (መግቢያ ተክቢራን) እያገኘ አርባ ቀን ጀመዐ የሰገደ ሰው ሁለት ነፃነት ይፃፍለታል። ከእሳትና ከንፍቅና ነፃ ይሆናል። |
| 18 | ሶላትን በጀመዓ መስገድ | ሶላትን በጀመዐ መስገድ ለብቻ ከመስገድ በ27 ደረጃ ይበልጣል። |
| 19 | የዒሻዕንና የሱብሒን ሶላቶች በጀመዐ መስገድ | የዒሻን ሶላት በጀመዐ የሰገደ ሰው ግማሽ ሌሊትን ቁሞ እንዳሳለፈው ይቆጠራል። የሱብሒን ሶላት በጀመዐ የሰገደ ሰው ሙሉ ሌሊትን ቁሞ እንዳሳለፈው የቆጠራል። |